# መመሪያ ቁጥር 1098/2017
# ጥራቱ የተገለጸ ዘር ማስፈጸሚያ መመሪያ

# Directive No 1098/2025
# Quality Declared Seed Directive

| መመሪያ ቁጥር 1098/2017<br>ጥራቱ የተገለጸ ዘር ማስፈጸሚያ መመሪያ | **Quality Declared Seed**<br>**Directive Number 1098/2025** |
|---|---|

| | |
|---|---|
| በፍጥነት እያደገ የመጣውን የአርሶ አደሩን እና ከፊል አርብቶ አደሩን የምርጥ ዘር ፍላጎት በመደበኛ ሥርዓት በሚቀርበው ዘር ብቻ ማሟላት ባለመቻሉ፤ | The increasing demand for improved seed by the farmers and semi-pasotralists cannot be met through the formal seed supply system alone; |
| ጥራቱ የተገለጸ ዘር ሥርዓት ተግባራዊ በማድረግ አማራጭ የዘር ጥራት ሥርዓት መዘርጋትና ይህ እውን እንዲሆን ዘር አምራች ከማሳና ከዘር ሎት 90 በመቶ የክልል ባለስልጣን 10 በመቶ ጥራት ማረጋገጥ የሚችሉበትን የአሰራር ሂደት መደንገግ በማስፈለጉ፤ | Implementing Quality Declared Seed as alternative quality control system with the modality 90 percent of seed quality assurance process, both at field and laboratory conditions, conducted by the producers and the remaining 10 percent by the regional authority; |
| አርሶ እና ከፊል አርብቶ አደሮች በአማራጭ የቁጥጥር ስርዓት ውስጥ ያለፈ ጥራቱ የተገለጸ ዘር መጠቀም እንዲችሉ በማስፈለጉ፤ | For farmers and semi-pastoralists to use quality declared seed that has passed through alternative seed certification system; |
| የግብርና ሚኒስቴር ስለዕፅዋት ዘር አዋጅ ቁጥር 1288/2015 አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2(ለ) እና አንቀጽ 29 ንዑስ አንቀጽ 2 በተደነገገው መሰረት ይህን መመሪያ አውጥቷል። | The Ministry of Agriculture, according to the Seed Proclamation No. 1288/2023 article 16 sub article 1 and 2(b) and Article 29 sub article 2, has issued this directive. |

# ክፍል አንድ
# ጠቅላላ

## 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "ጥራቱ የተገለጸ ዘር መመሪያ ቁጥር 1098/2017" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 2. ትርጉም

በአዋጅ ቁጥር 1288/2015 የተጠሰው ትርጓሜ እንደተጠበቀ ሆኖ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም ካልተሰጠው በቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1) **"የተመዘገበ ዝርያ"** ማለት በሃገሪቱ የዝርያ መልቀቅ ሥርዓት የሚጠይቀውን መስፈርት አሟልቶ በብሔራዊ የዝርያ አጽዳቂ ኮሚቴ እንዲባዛና እንዲመረት ፈቃድ ያገኘ ዝርያ ነው፤
2) **"መደበኛ የዘር ስርዓት"** ማለት የኢትዮጵያን የዘር ጥራት ደረጃ መስፈርት መሠረት የተመዘገበ የጸደቀ ዝርያ ዘር በዘር ጥራት ተቆጣጣሪ ተቋም አማካኝነት ሙሉ በሙሉ ከዝርያ መልቀቅ እስከ ግብይት ድረስ ቁጥጥር የሚደረግበት የአሠራር ሂደት ነው፤
3) **"የሚመረትበትና የሚሠራጭበት**

# Section One
# General

## 1. Short title

This directive may be cited as **"Quality Declared Seed Directive Number 2098/2025"**.

## 2. Definition

As the interpretation given in the proclamation 1288/2015 kept and unless the context of the term gives it a different meaning, in this directive:

1) "**Registered variety**" means a variety fulfilling the requirements of the country`s variety release system and got permission for multiplication and production by the national variety release committee.
2) "**Formal seed system**" means a process of quality control by the authority or regional authority according to the Ethiopian seed standards starting from the process of variety release to marketing.
3) "**Production and distribution**

አካባቢ" ማለት ክልሉ በወሰናቸው የዕጽዋት ዓይነቴዎች በአንድ ክልል ውስጥ ጥራቱ የተገለጸ ዘር የሚመረትበትና የሚሰራጭበት ስነምህዳር ነው፤

4) "ዘር አምራች" ማለት ጥራቱ የተገለጸ ዘር የሚያመርት ሰው ነው፤

5) "የዘር ሎት" ማለት በአካል ሊለይ የሚችል፣ የራሱ መለያ ያለውና መጠኑ የታወቀ የዘር ክምችት ነው፤

6) "የውስጥ የዕፅዋት ዘር ጥራት ቁጥጥር" ማለት ዘር አምራቹ የራሱን ማሳና የላቦራቶሪ ፍተሻን በራሱ ባለሙያዎች አማካኝነት የዘር ጥራት ደረጃ መስፈርትን መሠረት በማድረግ የሚያካሂደው ቁጥጥር ነው፤

7) "የውጭ የዕፅዋት ዘር ጥራት ተቆጣጣሪ" ማለት የተመዘገበ ዝርያ ዘር የሚያመርቱ አምራቾች በወጣው የመስክና የላቦራቶሪ የዘር ጥራት ደረጃ መስፈርት መሠረት ጠብቀው ማባዛታቸውን የሚቆጣጠርና ማረጋገጫ የሚሰጥ ህጋዊ ሰው ነው፤

8) "ኩታ ገጠም የዘር ማሳ" ማለት የጋራ ድንበር ያላቸው ሆነው

**location**" means plant species and agro-ecologies destined for production and distribution of quality declared seed by respective region.

4) "**Seed producer**" means a person who produces quality declared seed.

5) "**Seed lot**" means a known stored seed that can easily identified physically and has peculiar identifiers.

6) "**Internal Seed quality Control**" means the under taking of seed quality control at field and laboratory by the experts of the seed producer itself.

7) "**External seed inspector**" is a person who controls registered seed producers whether they conduct their seed production according to the set field and laboratory quality standards and issues certification.

8) "**Cluster seed field**" means a field planted with same kind of species,

ተመሳሳይ ሰብል፣ ዝርያ እና የዘር ደረጃ የተዘራባቸው ማሳዎችን ለዘር ማምረት ተግባር እንዲውል ማድረግ ነው፡፡

## 3. የተፈጻሚነት ወሰን

በአዋጁ አንቀጽ 3 ንዑስ አንቀጽ 2 ከ"ሀ" እስከ "ሐ" የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ይህ መመሪያ:-

1) በተሻጋሪ ርክበ ብናኝ በሚራባ የዕጽዋት ዝርያ፤
2) በመደበኛው የዘር ሥርዓት በመንግሥት ወይም በግል ዘር አምራችነት በተመዘገበ ሰው ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

## 4. ጥራቱ የተገለጸ ዘር መርሆዎች

1) አማራጭ የዘር ጥራት ማረጋገጥ ሥርዓት ማመቻቸት፣
2) ሙሉ በሙሉ በባለስልጣኑ ወይም በክልል ባለስልጣን ከሚደረገው ጥራት ማረጋገጥ ጎን ለጎን የሚሄድና የማይተካ፣
3) በመደበኛ የዘር ጥራት ማረጋገጥ ስርዓት በስፋት ያላተዳሰሱ የተለያዩ ሰብሎችን በጥራት ቁጥጥር ሂደት እንዲካተቱ ለማድረግ፣

variety and seed class intended for seed production.

## 3. Scope

Without prejudice the provisions declared under article 3 sub article 2 "a" and "c" of the proclamation this directive is not applicable on:

1) Plant variety with high level of outcrossing;
2) A person who is registered as formal seed system public or private seed producer.

## 4. Principles of quality declared seed

1) Provides alterative seed quality control system;
2) Do not substitutes the formal seed quality control system conducted by the authority and regional authority rather done side to side;
3) Incorporating crops that are not well-addressed by the formal seed quality control system;

4) የዘር ጥራት ማረጋገጥ ተደራሽነትን እውን ማድረግ፡፡

## ክፍል ሁለት

## የብቃት ማረጋገጫ አሰጣጥ

### 5. ጥራቱ የተገለጸ ዘር ለማምረት ብቃት ማረጋገጫ አሰጣጥ

ማንኛውም ሰው ጥራቱ የተገለጸ ዘር ለማምረት የሚያስችል ከክልል ባለስልጣን የብቃት ማረጋገጫ ለማግኘት የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት አለበት፤

1) ዘር የሚመረትበት ማሳ አጠቃላይ መስፈርት፣
   - ሀ) የኮንትራት፣ የኪራይ ወይም የባለቤትነት ህጋዊ ማስረጃ፤
   - ለ) ለዘር ማምረት አመቺ የሆነ፤
   - ሐ) በፌደራልና በክልል ደረጃ እውቅና ከተሰጣቸው አደገኛ አረሞችና በሽታዎች የጸዳ፤
   - መ) የሚገኝበት ስነምህዳር ሊመረት ለታቀደው ሰብል ተስማሚ የሆነ፤
   - ሠ) ከአጎራባች ማሳዎች የዘር ጥራት የሚያጓድሉ ምክንያቶች የሌሉ መሆኑን መረጋገጥ አለበት፤
   - ረ) ለጥራት ቁጥጥር፣ ለድጋፍና ክትትል አመቺ የሆነ መሆን አለበት።

4) To ensure seed quality accessibility.

## Part Two

## Issuance of competency certificate

### 5. Issuance of certificate of competency for quality declared seed production

Any person has to fulfill the below requirements to be issued certificate of competency by regional authority to engage in quality declared seed production:

1) Seed production farm requirements
   - a) Land ownership or rent or contract documents;
   - b) Suitable for seed production;
   - c) Free from ferederally and regionally declare noxious and soil born disease;
   - d) Agro-ecologically suitable to produce the selected plant species;
   - e) Ensure there are not contaminants that could compromise seed quality from neighbouring fields;
   - f) Accessible to quality control, support and supervision.

2) ኩታ ገጠም የማሣ ስፋት መስፈርት፡-

ሀ) ለብርዕ ሰብሎች ቢያንስ 3 ሄክታር፤

ለ) ለጥራጥሬና ለቅባት ሰብሎች ቢያንስ 2 ሄክታር፤

ሐ) ለአትክልትና መኖ ዘር ኩታገጠም የሆነ ማሣ በአንድ አካባቢ ቢያንስ 0.5 ሄክታር፤

መ) ለኮረት፣ ለቁርጥራጭ ኩታ ገጠም የሆነ ማሣ በአንድ አካባቢ ቢያንስ 1 ሄክታር፤

ሠ) ለፍራፍሬ እና ለአነቃቂ ሰብሎች መሠረተ ግንድ ዝግጅት የሚሆን ማሳ ቢያንስ 0.5 ሄክታር መሆን አለበት፡፡

2) Cluster farm area requirement:

a) At least 3 hectares for cereal crops;

b) At least 2 hectares for pulses and oil crops;

c) At least 0.5 hectares for vegetables and forages;

d) At least 1 hectare for bulb, tubers and cuttings;

e) At least 0.5 hectares of land in one area for fruit and stimulant crops root stock.

3) በተክል ብዛት መስፈርት በተመለከተ፡-

ሀ) ለመከተብ ወይም እንቡጥ ወይም ሳዮን ቢያንስ 5 እናት ተክል፣

ለ) ለኮርም ቢያንስ 100 ተክል፣

ሐ) ለቡና ዘር አቅራቢነት ከሆነ ቢያንስ 750 ተክል በቡድን፣

መ) ለደን ዘር መልቀም የሚሆን 25 እናት ዛፍ ያለው መሆን አለበት፤

3) Requirements on plant number basis:

a) At least 5 mother plants for bud or scion or grafting;

b) At least 100 mother trees for corm;

c) At least 750 mother trees for coffee seed supplier;

d) At least 25 mother trees for forest seed collection.

4) ችግኝ ጣቢያን በተመለከተ የኢትዮጵያን የችግኝ ጣቢያ ደረጃ ያሟላ፤

4) For nursery, according to nursery standard of the country.

5) የእርሻ መሣሪያዎች በባለስልጣኑ እና ክልል ባለስልጣን ስምምነት በተዘጋጀ ቅጽ በሚዘረዘረው መሰረት ሊያቀርብ የሚችል፣

6) በዚህ መመሪያ ዕዝል 1 የተገለጸውን መስፈርት ያሟላ የዘር መጋዝን የባለቤትነት ማረጋገጫ ሰነድ ወይም በኪራይ ስለማግኘቱ ህጋዊ ማረጋገጫ የሚያቀርብ፣

7) የውስጥ የጥራት ቁጥጥር ሥርዓት ያለው ወይም አገልግሎቱን ከሌላ አካል ስለማግኘቱ ህጋዊ ማረጋገጫ ማቅረብ የሚችል።

## 6. የውስጥ ጥራት ቁጥጥር ይዘት

1) ማንኛውም ጥራቱ የተገለጸ ዘር አምራች የውስጥ የመስክና የላቦራቶሪ ጥራት ቁጥጥር ሊኖረው ይገባል፤

2) የመስክ ጥራት ቁጥጥር ለማካሄድ የሚያስፈልጉ ኮምፓንዲኒየም፣ አንድ ካሬ ሜትር ከእንጨት ወይም ከብረት የተሠራ ኳድራንት፣ መቁጠሪያ፣ ጂ.ፒ.ኤስ፣ የዘር እርጥበት መለኪያ፣ አነስተኛ የማጉያ መነጽር፣ ከከረጢት ወይም ከወረቀት የተሠራናሙና መያዣ፣ ፕላስቲክ፣ የምድር ሚዛን ያለው

5) Provides farm implements according to the format developed based on the consensus of the authority and regional authority.

6) Able to provide proof of the seed storage ownership or rent that fulfils the requirements set in accordance of Annex 1 of this directive.

7) Has own internal quality control system or can provide proof of obtaining the service from another party.

## 6. Features of internal control system

1) Any seed producer should have internal field and laboratory quality control system;

2) Should have own or able to get materials for field quality control, including compendium, 1 meter square quadrant made from wood or steel, counter, GPS, moisture tester, magnifying lens, sample holder made of paper or plastic, balance;

ወይም በትውስት ወይም በሶስተኛ ወገን ድጋፍ ማግኘት የሚችል መሆን አለበት፤

3) በአምራቹ አቅም ሥራው በላቦራቶሪ የውስጥ ጥራት ቁጥጥር የሚከናወን ከሆነ ቢያንስ ራሱን የቻለና 9 ካሬ ሜትር ያለው ክፍል፣ የናሙና መውሰጃ መቀሸቢያ፤ የዘር ንጽህና መሣሪያ ቁሳቁሶች እንደ አናሌቲካል ሚዛን፣ ጠረጴዛ፣ አጉሊ መነጽር፣ ፎርሴፕስ፣ ስፓቹላ፣ የዘር ብቅለት መፈተሻ፣ የዘር ማብቀያ ፕላስቲክ ሣህኖች የሚያሟላ መሆን አለበት፤

4) በራሱ አቅም ማሟላት የማይችል ከሆነ ግን የዘር ፍተሻ ላቦራቶሪ አገልግሎት ሊሰጡ ከሚችሉ ተቋማት አገልግሎቱን ማግኘት እንደሚቻል የሚያረጋግጥ ማስረጃ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

7. **ጥራቱ የተገለጸ ዘር ለማዘጋጀት መሟላት ያለበት መስፈርት**

1) በዚህ መመሪያ ዕዝል 1 የተገለጸውን መስፈርት ያሟላ የዘር መጋዝን የባለቤትነት ማረጋገጫ ሰነድ ወይም በኪራይ ስለማግኘቱ ህጋዊ ማረጋገጫ የሚያቀርብ፣

2) የዘር ማበጠሪያ መሣሪያ ያለው

3) If seed producer has own seed laboratory to conduct seed quality testing, the laboratory should have a minimum area of 9 meter square; sampling device, physical seed quality testing facilities and analytical balance, table, magnifying glass, forceps, spatula, germination bowl;

4) If seed producer is unable to provide own laboratory requirement, should provide evidence for obtaining the service from other parties.

7. **Requirements for quality declared seed processing**

1) Owns a seed storage that fulfil requirements described under annex 1 of this Directive or able to get in rent and submit legal document for both;

2) Owns seed cleaning machine or able to clean the seed using human labor;

ወይም የሰው ኃይል አሰማርቶ ማስበጠር የሚችል፣

3) የማሸጊያ ማሽን ያለው ወይም ከሌላ አካል በኪራይ ወይም በትውስት ስለማግኘቱ ማረጋገጫ ማቅረብ የሚችል፣

4) በዘር ዝግጅት ቢያንስ የአንድ ሳምንት ሥልጠና የወሰደ ስለመሆኑ ወይም የአንድ ወር ልምድ ያለው መሆኑን ማስረጃ ማቅረብ አለበት።

8. **ጥራቱ የተገለጸ ዘር ለማምረት ወይም ለማሠራጨት የማመልከቻ አቀራረብ ሂደት**

1) አመልካቹ ጥያቄውን በክልል ባለስልጣኑ በተዘጋጀው ቅጽ መሠረት ሞልቶ ለክልል ባለስልጣን ማቅረብ አለበት፤

2) የክልል ባለስልጣን አመልካቹ የዘመኑ ዘር አምራቾች ዝርዝር ውስጥ ስለመካተቱ መርምሮ ማረጋገጥ አለበት፤

3) አመልካቹ ሊያመርተው የሚፈልገውን ሰብል በዝርያ መዝገብ መስፈሩን የክልል ባለስልጣን ማረጋገጥ አለበት፤

3) Owns a packaging machine or able to get in rent, or borrowing and submit legal document for both;

4) Should have provide evidence that a person has received at least one week of training in seed processing or has one month experience in seed processing.

8. **Application proceedures for the prodution and distribution of quality declared seed**

1) The applicant shall submit the request using the application form prepared by the regional authority;

2) The regional authority shall verify whether the applicant is included in the list of eligible seed producers;

3) The regional authority shall verify whether the crop variety that the applicant wish to grow in the variety registry;

4) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 5 መሰረት ጥራቱ የተገለጸ ዘር ለማምረት ስለ ብቃት ማረጋገጫ አሰጣጥ የተዘረዘርውን መስፈርት ማሟላቱን የክልል ባለስልጣን ማረጋገጥ አለበት፡፡

## ክፍል ሶስት
## ዘር ማምረት፣ ማዘጋጀትና ጥራት ማረጋጋጥ

**9. የጥራት ማረጋገጥ አገልግሎት ስለመጠየቅና ስለመተግበር**

1) አመልካቹ የዘር ጥራት ቁጥጥር አገልግሎት ለማግኘት ለክልል ባለስልጣን ጥያቄ ያቀርባል፣

2) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 መሰረት ጥያቄው ተቀባይነት ሲያገኝ የዘር ማምረትና ዝግጅት ስራ በአንቀጽ 11 ንዑስ አንቀጽ 3 በተዘረዘረው መሰረት ማከናወን አለበት፡፡

**10. ጥራቱ የተገለጸ ዘር ለማምረት ስለሚውል የዘር ምንጭ**

1) ጥራቱ የተገለጸ ዘር ለማምረት የሚውል የዘር ምንጭ በዘር ጥራት

4) The regional authority shall ensure whether the applicant fulfils the requirements set out in article 5 of this directive for issuance of certificate of competency for the production of quality declared seed.

## Part Three
## Seed production, processing and quality control

**9. Requesting and executing quality assurance services**

1) The applicant submits a request to the regional authority for seed quality control services;

2) When the request is accepted in accordance with sub article 1 of this article, the seed production and processing task should be conducted as per the provisions stated in article 11 sub article 3.

**10. Seed source to produce quality declared seed**

1) The seed source used to produce quality declared seed shall be a seed

ደረጃ ዝርዝር የተገለጸው የዘር ትወልድ ነው፤

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ የተለቀቀ ዝርያ ለሌላቸው የሰብል፣ የመኖ፣ የሆርቲካልቸርና የደን ዓይነቶች ነባር ዝርያ ሆኖ በክልሉ ባለስልጣን ለዘር ምንጭነት እንዲያገለግል እውቅና የተሰጠውን መጠቀም ይቻላል፡፡

## 11. ጥራት መቆጣጠርና ማረጋገጥ

1) ጥራቱ የተገለጸ ዘርን ጥራት የማረጋገጥ ሥራ በአምራቹና ጥራትን ማረጋገጥ ኃላፊነት በተሰጠው የክልል ባለሥልጣን ተፈጻሚ ይሆናል፤

2) ጥራቱ ለተገለጸ ዘር ሥርዓት በወጣው የዘር ጥራት ደረጃ መሠረት ይከናወናል፤

3) በመስክ ላይ ጥራቱ የተገለጸ ዘር ሲረጋገጥ፡-

   ሀ) ጥራቱ በተገለጸ የዘር ጥራት ደረጃ መሰረት ተፈጻሚ መሆን አለበት፤

   ለ) ቢያንስ አስር በመቶኛ በሚሆነው ማሣ ላይ በክልል ባለስልጣን ቁጥጥር ይካሄዳል፤

class that described in the seed quality standards;

2) Without prejudice sub article 1 of this article, local variety seed can be used as source seed to produce quality declared seed for crops or forage or horticultural or forest species that lack released varieties.

## 11. Seed quality control and assurance

1) Seed quality approval of quality declared is a shared responsibility of the seed producer and the regional authority;

2) The quality declared system shall be performed according to the specific seed quality standards;

3) Quality declared seed is verified in the field:

   a) Shall be conducted as per quality declared seed standard;

   b) At least 10% of the seed farm shall be controlled by the regional authority;

ሐ) በአሥር መቶኛው የሚገኘው ውጤት በቀሪው ማሣ ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፤

መ) የአስር በመቶኛው የጥራት ቁጥጥር ሂደት በመደበኛው የማሣ ጥራት ቁጥጥርና ማረጋገጥ አፈጻጸም ሂደት መሠረት ይከናወናል፡፡

4) በላብራቶሪ ጥራቱ የተገለጸ ዘር ሲረጋገጥ፡-

ሀ) የዘር ናሙና የሚወሰደው የመስክ ጥራት አሟልቶ በክልሉ ባለስልጣን ካለፈ ማሣ የተመረተ ዘር ላይ መሆን አለበት፣

ለ) የዘር አከመቻቸት እና ናሙና አወሳሰድ በዘር ናሙና አወሳሰድ መስፈርት መሠረት መሆን አለበት፣

ሐ) የክልል ባለስልጣን ጥራቱ በተገለጸ ዘር ተዘጋጅቶ በሎት ከተደረደረው ውስጥ ከጠቅላላው ሎት ቢያንስ 10 በመቶኛ ከሚሆነው ናሙና መውሰድ አለበት፣

መ) የናሙና አወሳሰድና የላቦራቶሪ ፍተሻ ሂደቱ ከመደበኛው የዘር

c) The results from the 10% shall be applied to the remaining field;

d) The 10% quality control process should be in accordance with the procedures set to the formal seed production process.

4) When confirming the quality declared seed in the laboratory:

a) Seed sample taken should be from the field that have been passed the field inspection by the regional authority;

b) Seed lots and sampling shall be done according to the formal procedures;

c) The regional authority shall draw sample from 10% of the total seed lot;

d) The sampling and laboratory testing process should be similar to that of formal seed quality

ጥራት ማረጋገጥ ጋር ተመሳሳይ በሆነ መልኩ መሆን አለበት፣

ሠ) በአሥር መቶኛው የሚገኘው ውጤት በቀሪው 90 በመቶኛው ሎት ላይ መሆን አለበት፣

ረ) ጥራቱ የተገለጸ ዘር ጥቅም ላይ ሳይውል ካደረ ናሙና የሚወሰደው ከሁሉም ሎቶች ይሆንና ውሳኔ የሚሰጠው ግን ጥራቱ በተገለጸ ዘር የጥራት ደረጃ መሠረት መሆን አለበት፡፡

assurance;

e) The results from the 10% shall be applied to the remaining 90% seed lots;

f) If there is carryover seed of quality declared, samples shall be taken from all seed lots and decision shall be made according to the quality declared seed standards.

## 12. ማሸግና መለያ ምልክት ስለማድረግ

1) ዘሩ ከተበጠረ በኋላ የአምራቹ መለያ ምልክት ከውስጥና ከውጭ በማድረግ እንዲሁም የክልል ባለስልጣን መለያ ምልክት በግልፅ በሚለይ መልኩ ከውጭ ብቻ በማድረግ የጥራት ደረጃውን በጠበቀ ከረጢት መታሸግ አለበት፣
2) የመለያ ምልክቱ በዚህ መመሪያ ዕዝል 2 የተዘረዘሩት መረጃዎች ያካተተ እና አንዴ ጥቅም ላይ ከዋለ በኋላ እንደገና ጥቅም ላይ እንዳይውል ተደርጎ መዘጋጀት አለበት፣

## 12. Packaging and labeling

1) Once the seed is cleaned, the seed should be packed in standard packaging materials, and the producer's label should be put on the inside and outside and the regional authority's label clearly visible only on the outside of the bag.
2) The label should include the information listed according to annex 2 of this article and must be prepared so that once used, cannot be reused.

3) መለያዎች ሲዘጋጁ በቅርጽ ሬክታንግል ሆነው የሚከተሉትን የቀለም ቅንብር ሊይዙ ይገባል፡

ሀ) ጥራቱ ለተገለጸ ዘር አንደኛ ትውልድ መደቡ አረንጓዴ ቀለም፣

ለ) ጥራቱ ለተገለጸ ዘር ሁለተኛ ትውልድና ከዚያ በላይ መደቡ ሙሉ ለሙሉ ቢጫ ቀለም፣

ሐ) ለሁሉም የዘር ደረጃ የመለያው አንዱ ጫፍ ከሌላው የሚለይ ቀለም ዝቅተኛው ርቀት 3 ሴ.ሜ በመጠበቅ ጥቁር ቀለም፡፡

4) የሎት መለያ ቁጥር አጻጻፍ

ሀ) የተመረመረበት ዓመት፣

ለ) የድርጅቱ የምዝገባ ቁጥር፣

ሐ) የሰብል ዓይነት፤

መ) የማሣ ቁጥር፣

ሠ) የዘር ትውልድ ደረጃ፣

ረ) የሎት ቁጥር ማካተት አለበት፡፡

## 13. በመጋዝን ወስጥ የዘር ሎት አደራደር

በመጋዝን ውስጥ ዘር ሎት አደራደር በሚከተለው መስፈርት መሰረት መሆን አለበት፡-

1) የዘር አደራደሩ ለናሙና አወሳሰድ አመቺ እንዲሆን፤ በግድግዳና

3) Labels shall be rectangle in shape and have the following color scheme:

a) Quality declared seed 1 is green in color;

b) Quality declared seed 2 and subsequent generations should be yellow in color;

c) For all seed classes, a minimum distance of 3 cm from one end of the label to the other with black color label.

4) Contents of lot reference number

a) Year of production

b) Seed producer's registration number

c) Crop type

d) Farm number

e) Seed class

f) Lot number

## 13. Seed lots arrangement in the store

Seed lots arrangement in the store shall be in the following criteria

1) Convenient for sampling; the distance between the lots and the

በሎት መካከል፣ እንዲሁም በየሎቱ መካከል ያለው ርቀት፤ ናሙና ለሚወስደው ሰው በቂ መዘዋወሪያ እንዲያገኝ የሚያስችል፣

2) ዘሩን ከዕርጥበትና ከተባይ ለመከላከል እንዲያስችል ከወለሉ በላይ መደርደሪያ ወይም ርብራብ ያለው፤

3) በዚህ መመሪያ ዕዝል 1 መሰረት በናሙና አወሳሰድ አመቺ በሚሆን መልኩ የተዘጋጀ መሆን አለበት፡፡

distance between the walls should allow the seed sampler to move around sufficiently;

2) Have pallet above the floor to protect the seed from moisture and pests;

3) Should be convenient for seed sampling in accordance with annex 1 of this directive.

## 14. የላብራቶሪ ውጤት ስለማሳወቅ

1) የክልል ባለስልጣን የላቦራቶሪ ፍተሻ ውጤቱ ለአምራቹ በደብዳቤ ይገለጻል፣
2) ውጤቱ ከመገለጹ በፊት ዘሩን ለተጠቃሚ ማሰራጨት አይቻልም፤

3) ከመስፈርቱ በታች የሆነ የዘር ሎት “ለዘርነት የማይውል” በሚል በሎቱ ላይ ይገለጻል።

## 14. Reporting laboratory results

1) The regional authority shall write a letter of the laboratory testing result to the seed producer.

2) The seed cannot be distributed to users before the result is announced.

3) A seed lot below the standard should be marked as “not use for seed” on the lot.

## 15. ጥራቱ የተገለጸ ዘር ግብይት፤

1) ጥራቱ የተገለጸ ዘር ለግብይት የሚቀርበው በተመረተበት አካባቢ

## 15. Quality declared seed marketing

1) Quality declared seed shall be marketed within the vicinity of its

ነው፤

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ:-

ሀ) በክልል ውስጥ ከአንድ አካባቢ ወደ ሌላ አካባቢ በሚዛወርበት ወቅት በክልል ውሳኔ ተፈጻሚ ይሆናል፤

ለ) ከአንድ ክልል ወደ ሌላ ክልል ጥራቱ የተገለጸ ዘር ለመዘዋወር ተጠቃሚው ክልል በሚያቀርበው ፍላጎት እና ውሳኔ መሰረት ተፈጻሚ የሚሆን ነው፡፡

3) የዘር ግብይት መረጃ ለግብርና ጽ/ቤት ለሚመለከተውና ዘሩ በተመረተበት አካባቢ ለሚገኝ አካል በወቅቱ ሪፖርት ማቅረብ አለበት፡፡

## ክፍል አራት
## ተግባርና ኃላፊነት

### 16. የባለስልጣኑ ተግባርና ኃላፊነት

ጥራቱ የተገለጸ ዘር ሥርዓት ተግባራዊ ለማድረግ ባለስልጣኑ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት አለበት፡-

1) ጥራቱ የተገለጸ ዘር ሥርዓት ሀገራዊ መጣጣም እንዲኖረው ሀገራዊ

area of production.

2) Without prejudice sub article 1 of this article:

a) Seed movement from one location to another location within the same region shall be determined by the region;

b) The movement of quality declared seed from one region to another shall be done based on the request and decision of the demanding region.

3) Seed marketing data shall timely be submitted to agriculture office and other concerned bodies found in areas where the seed produced.

## Section Four
## Duty and responsibility

### 16. Duty and responsibility of the authority

To ensure the implementation of the quality declared seed, the authority shall have the following duty and responsibility:

1) Shall organize and coordinate the national platforms for harmonization of quality declared seed system at

የምክክር መድረኮችን ማደራጀት፣ ማስተባበር፣

2) ጥራቱ የተገለጸ ዘር ሥርዓቱ የመደበኛውን የዘር ማምረትንና ግብይት ስርዓት ክፍተት በሚያሟላ መልኩ እንዲተገበር ይከታተላል፣ ይገመግማል፣ ክፍተት ሲኖር ከቢሮና ከክልል ባለሥልጣን ጋር በመመካከር ማስተካከያ እርምጃ የመውሰድ፣

3) ጥራቱ የተገለጸ ዘር ሥርዓትን ተፈጻሚ ለማድረግ በሀገር አቀፍ ደረጃ የአቅም ግንባታ ሥራ የመስራት፡፡

## 17. የክልል ባለስልጣን ተግባርና ኃላፊነት

ጥራቱ የተገለጸ ዘር ሥርዓት ተግባራዊ ለማድረግ የክልል ባለስልጣን የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት አለበት፡-

1) ቢሮው ጥራቱ የተገለጸ ዘር ሥርዓት እንዲተገበርባቸው የሚፈልገውን አካባቢ፣ የሰብል ዓይነቱ እንዲወስን እና ዝርዝር እቅድ እንዲያዘጋጅ ድጋፍ የማድረግ፣

2) ጥራቱ የተገለጸ ዘር ሥርዓትን በቢሮው ውሳኔ መሰረት የማስተባበር፣

the county level;

2) Monitors and evaluates for the proper implementation of the quality declared seed system complementary to the formal seed production system; and shall take corrective measures in consultation with bureau and regional authority;

3) Shall conduct capacity building activities at the national level to properly implement the quality declared seed system.

## 17. Duty and responsibility of the regional authority

To ensure the implementation of the quality declared seed, the authority shall have the following duty and responsibility:

1) Shall support the Bureau to identify areas for implementation of the seed quality declare seed system, crop species and in the preparation of detail plan;

2) Coordinates the quality declared seed system in accordance with the decision of the bureau;

3) በቢሮው በተወሰኑ አካባቢና የሰበል ዓይነቱ በሥርዓቱ የሚሳተፍ አምራችን የመወሰን፣ ማመልከቻና ማስረጃ የመመርመር፣ የማረጋገጥ፣ የመመዝገብ፣ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የመስጥት፣ የማደስ፣ የማገድ፣ የመሰረዝ፣

4) ጥራቱ የተገለጸ ዘር አመራረትንና ግብይትን ጥራት የመቆጣጠር፣ የማስተዳደር፣

5) ጥራቱ የተገለጸ ዘር ስርዓት ተፈጻሚ እንዲሆን በክልሉ ስር ለሚገኙ ለባለ ድረሻ አካላት እቅም የመገንባት።

## 18. የቢሮ ተግባርና ኃላፊነት

ጥራቱ የተገለጸ ዘር ሥርዓት ተግባራዊ ለማድረግ ቢሮ ወይም በየደረጃው ያለ የቢሮ መዋቅር የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት አለበት፡-

1) ጥራቱ በተገለጸ ዘር ብዜት ለሚሰማራ አምራች የሙያና የሎጀስቲክ ድጋፍ ይሰጣል፣

2) በክልሉ ባለስልጣን ትብብር በተጠየቀ ጊዜ ጥራቱ ተገለጸ ዘር ቁጥጥር ስራን ያከናውናል፡፡

3) Identify seed producer wishes to engage in quality declared seed production in areas and crop species decided by the bureau; evaluate and ensure the application, register, issue certificate of competency, renew, suspend, revoke;

4) Administer and control quality declared seed production and marketing;

5) Shall conduct capacity building activities at the regional level to properly implement the quality declared seed system.

## 18. Duty and responsibility of the bureau

To ensure the implementation of the quality declared seed, the bureau shall have the following duty and responsibility:

1) Provide professional and logistical support to producers engaged in quality declared seed production;

2) When requested by the regional authority, provide quality declared seed inspection.

**19. የዘር አምራች ወይም አዘጋጅ ተግባርና ኃላፊነት**

ጥራቱ የተገለጸ ዘር ሥርዓት ተግባራዊ ለማድረግ የዘር አምራች ወይም አዘጋጅ የሚከተሉት ኃላፊነትና ተግባር አለበት፡-

1) በመስክ ደረጃ የዘር ጥራት ቁጥጥር ወይም ኢንስፔክሽን ከተደረገ በኋላ ሊወገዱ ወይም ሊስተካከሉ የሚገባቸው ጉዳዮችን ተከታትሎ የመፈጸም፣
2) የጥራት ቁጥጥሩን ያለፉ ማሳዎች ሰብልን ለመሰብሰብ ትክክለኛው የዘር እርጥበት መጠን ደረጃ መድረሱን የማረጋገጥ፣
3) የጥራት ደረጃን ሳያሟሉ ከወደቁ ማሣዎች ዘር እንዳይሰበሰብ ኃላፊነት ወስዶ የመስራት፣
4) ተቀባይነት ካገኙ ማሣዎች ዘር በወቅቱ ሰብስቦ የውቂያ ተግባራትን የመፈጸም፣
5) የተወቃውን ዘር አበጥሮ በተገቢ ከረጢት ያሽጋል፣ የሎት አደራደርን ተከትሎ የማከማቸት፣
6) ክምችቱን ተከትሎ ናሙና እንዲወሰድለት ለክልል ባለስልጣኑ ጥያቄ የማቅረብ፣
7) ለዘርነት እንዳይውሉ በክልል

**19. Duty and responsibility of seed producer and processor**

To ensure the implementation of the quality declared seed, the authority shall have the following duty and responsibility:

1) Implements issues that need to be addressed or corrected after field-level seed quality control or inspection;
2) Shall ensure the correct moisture meter for harvesting crops from fields that have passed the quality control;
3) Shall take the responsibility for not collecting seeds from rejected fields;
4) Shall collect seeds from accepted fields and trashed;
5) Shall process the seeds, packed and store as per the seed lots standards;
6) Shall request the regional authority to take sample;
7) Shall take the responsibility for not

ባለስልጣን ውሳኔ የተሰጠባቸውን የዘር ሎቶች በሥርጭት ሥርዓቱ እንዳይካተቱ ኃላፊነት ወስዶ የመስራት፡፡

## ክፍል አምስት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 20. ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው መመሪያዎች

በግብርና ሚንስቴር የወጣው ጥራቱ የተገለጸ ዘር ሥርዓት ማስፈጸሚያ መመሪያ ቁጥር 839/2007 በዚህ መመሪያ ተሽሯል፡፡

### 21. መመሪያው የመፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በግብርና ሚኒስቴር ሚኒስትር ተፈርሞ በፍትሕ ሚኒስቴር ተመዝግቦ በሚኒስቴሩ እና በራሱ በፍትሕ ሚኒስቴር ድረ-ገፅ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

ግርማ አመንቴ (ፒ.ኤች.ዲ)
ሚኒስትር
የግብርና ሚኒስቴር
አዲስ አበባ

distributing the rejected seed lots by the regional authority.

## Section Five
## Miscellaneous provisions

### 20. Repealed directives

Quality Declared Seed System Directive Number 839/2007, endorsed by the Ministry of Agriculture, is repealed by this directive.

### 21. Date of enforcement of this directive

This directive shall be applicable on the date it is signed by the minister, register with the Ministry of Justice and posted on the Ministry of Justice website.

Girma Amente (PhD)
Minister
Ministry of Agriculture
Addis Ababa

**ዕዝል 1፡ የመጋዝን መስፈርት**

1. መጋዘን

ዘር ከተዘጋጀ በኋላ በዘር ሎት ስርዓት ለማከማቸት የሚያስችልና የሚከተሉት መስፈርቶችን ያሟላ መጋዘን ያለው፡-

1) ህንፃ፡-

ሀ) ህንፃው ከድንጋይ ወይም ከሸክላ ወይም ከብሎኬት ወይም ከጭቃ ግድግዳ የተሰራ አራት ማእዘን ቅርጽ የሆነ፤

ለ) ከጭቃ የተሰራ ግድግዳ በውስጥና በውጭ በሲሚንቶ የተለሰነ፤

ሐ) የህንፃው አቀማመጥ ከምእራብ ወደ ምስራቅ አቅጣጫ የተገነባ ሊሆን ይገባል፡፡

2) ጣሪያ፡-

ሀ) ደጋፊ ምሶሶዎች ለድርድር እና ለጽዳት እንዳያስቸግር እንዲሁም ተባይ መግቢያና መደበቂያ በማይሆኑበት ሁኔታ መሠራት ይኖርባቸዋል፤

ለ) ጣሪያው ውሀ ፍጹም የማያስገባ መሆን አለበት፤

ሐ) ለዘር ሎት ድርዳሮ ተገቢው ቦታና ከፍታ እንዲኖር ለማስቻል የጣሪያው ጫፍ ከመሬት በላይ ቢያንስ 5 ሜትር ከፍታ ሊኖረው ይገባል፤

**Annex 1: Storage Requirements**

**1. Storage**

Following seed processing, the storage shall fulfill the following requirements:

1) The building

a) The building shall be rectangular in shape, made of stone or clay or blocket or mud walls;

b) A wall made of mud should be cemented both from inside and outside;

c) The layout of the building should be from west to east.

2) Roof

a) Support pillars should be constructed in such a way that they are not possing difficulty for storing and cleaning, and they don`t become enterance and hiding place of insects;

b) The roof must be completely waterproof;

c) The top of the roof should be at least 5 meters above the ground to allow proper space and height for the seed lot arrangement;

3) ግድግዳ፡-

ሀ) የግድግዳ ስንጥቅጥቆች የቆሻሻ ማጠራቀሚያና የተባይ እንቁላል መጣያ እንዳይሆን መደፈንና መለሰን አለበት፤

ለ) ጣሪያና ግድግዳው ከ6 ሚ.ሊ ሜትር ባልበለጠ ክፍተት መገንባት ይኖርበታል፤ ወፎች ጎጆ ሊሰሩ የሚችሉበት ምንም አይነት ጠርዝ መኖር የለበትም፤

ሐ) የውስጥ ብርሃን እንዲኖረው የውስጥ ግድግዳ ነጣ ያለ ቀለም መቀባት አለበት፤

መ) የግድግዳው ቀለም ሲታጠብ በቀላሉ የማይለቅ መሆን አለበት፡፡

4) በር፡-

ሀ) የዘር መጋዘን በሮች በአንዱ የግድግዳ ፊት ለፊት ገጽ ሆነው እንደ አስፈላጊነቱ ከአንድ እስከ ሁለት ትላልቅ በሮች ይኖሩታል፤

ለ) እንደ አስፈላጊነቱ ሁሉም ትላልቅ በሮች ተንሸራተው የሚዘጉና አይጥ እንዳይሾልክ የመንሸራተቻው አቃፊ በብረት የታሸገ እና በሁሉም አቅጣጫ (ከጎን ከታችና ከላይ) የግጣሙ

3) Wall

a) Wall cracks should be sealed and cemented to avoid garbage and insect egg laying place;

b) The ceiling and the top of wall should be built with no more than 6 mm space. There should be no edges where birds can nest;

c) Interior walls should be painted white to have interior light.

d) The wall paint should not come off easily when washed.

4) The door

a) As deemed necessary, the seed storage shall have one or two large doors, one at the front face of the wall;

b) As required, all large doors should easily slide and close; to prevent mice from crawling in, the sliding folder should be lined with metal and the gap in all directions (sides, bottom and top)

ክፍተት ከ6 ሚሊ ሜትር የማይበልጥ መሆን ይኖርበታል፤

ሐ) በሩ ዝገትን ለመከላከል በበቂ የመጀመሪያ እና መጨረሻ ሽፋን ቅብ መቀባት ይኖርበታል፤

መ) የበሩ አቃፊ ከድንገተኛ የግጭት አደጋ ለመከላከል ከ10-15 ሴንቲ ሜትር ዲያሜትር ባለው የብረት ቧንቧ የተሰራ መከላከያ ሊኖረው ይገባል፡፡

5) ወለል፡-

ሀ) ወለሉ እርጥበት በማያሳልፍ እና በክብደት የተነሳ በቀላሉ ከማይሰባበር ኮንክሪት የተዘጋጀ ሊሆን ይገባል፤

ለ) እርጥበትን ለመከላከል ከወለሉ በላይ ፓሌት /ርብራብ/ ሊኖረው ይገባል፡፡

6) ብርሀን፡-

የመጋዘን ብርሃን በዘር መያዣ ከረጢት ላይ ያለውን መለያ ምልክቶች ወይም መረጃዎችን ማየት በሚያስችል ሁኔታ

ሀ) የመጋዘን ጣሪያው አልፎ አልፎ ብርሃን አስተላላፊ ነጭ ቆርቆሮ የተሰራ መሆን ይኖርበታል፤

should not be more than 6 mm;

c) The door should be painted with sufficient first (primer) and final (enamel) coating to prevent corrosion;

d) The door frame should be protected by a 10-15 cm diameter steel pipe to prevent accidental collisions

5) Floor

a) The floor should be made of concrete that is impervious to moisture and does not break easily due to heavy weight;

b) It should have a pallet above the floor to prevent moisture

6) Light

To ensure that the storage light is sufficient enough to read information on tags of seed bags,

a) The roof of the warehouse should include translucent white sheets.

ለ) መብራቶች ከፍሎረሰንት የተሰሩ መሆንና ከግድግዳ በላይ በኮርኒስ ከፍታ ልክ መገጠም ይኖርበታል፤

ሐ) ማብሪያና ማጥፊያው ከመግቢያ በሩ አካባቢ መሆን ይኖርበታል፡፡

7) የአየር ዝውውር

እንደ ስነምህዳሩ ሁኔታ የህንፃውን የላይኛው ሞቃት አየርና የወለሉን እርጥብ አየር ከመጋዘን ውስጥ ለማስወገድ፡-

ሀ) የአየር መቅዘፊያ እንደየመጋዘኑ ስፋት በአማካይ ቦታ የተገጠመለት፤

ለ) ከ6 ሚሊ ሜትር ወንፊት የተሰራ የአየር ማናፈሻ ቀዳዳ በጥንድ መልኩ ከመጋዘኑ ፊትና ኋላ በትይዩ በየ2 ሜትር ርቀት ሊኖረው ይገባል፤

ሐ) በግድግዳው የላይኛው ጫፍ ያለ የአየር ማናፈሻ ቀዳዳ ዝናብ በማያስገባ መልኩ ክፍት መሆን አለበት፤

8) የእሳት አደጋ መቆጣጠሪያ

በዘር ማከማቻ መጋዘን ውስጥና አካባቢ ሊከሰት የሚችልን እሳት አደጋ ለመቆጣጠር መጋዘኑ የእሳት ማጥፊያ በየበሩ የተገጠመለት

b) Lights should be made of fluorescent and installed above the wall at the same height as the ceiling.

c) The switch should be near the entrance.

7) Air movement

To ensure removal of top hot air of the building and floor moisture from the storage:

a) An exhaust fan is installed at an average location depending on the size of the storage;

b) A ventilation hole, made of 6 mm mesh, should be spaced in pairs at 2 meter intervals parallel to the front and back of the storage;

c) A ventilation opening, at the upper end of the wall, should be open with assurance of avoiding rain from entering into the store.

8) Fire Extinguisher

In order to control the risk of fire that may occur in and around the seed store, the storage should have a fire extinguisher installed at each

በየጊዜው የሚታደስ ሊሆን ይገባል፤

9) ምዝን የአየር እርጥበት እና የሙቀት መጠን መለኪያ የተገጠመለት፤

10) መጫኛ/ማራገፊያ

የመጋዘኑ መጫኛና ማራገፊያ የሚከተሉትን መስፈርቶች ያሟላ መሆን አለበት፡-

ሀ) በመጠለያ የተሸፈነ መጫኛ/ማራገፊያ ሥፍራ በበሩ መኖር አለበት፣

ለ) በእጅ ለሚገፉ ጋሪዎች ለፎርክ ሊፍት ሊያገለግል የሚችል ተዳፋትነት ያለው መንገድ በአንድ በር ላይ ብቻ እንዲኖር ያስፈልጋል፤

ሐ) የጭነት መኪናዎች የዘር መጋዘንና የዘር ክምችትን ሊያበላሹ ስለሚችሉ ወደ መጋዘን መግባት የለባቸውም፤

11) የመጋዘን ስፋት መጠን፤

ሀ) በስታንዳርድ የተወሰነ የዘር ሎት መጠን፤

ለ) በአራቱም አቅጣጫ ከግድግዳ እስከ ሎት አንድ ሜትር

ሐ) በሎት እና በሎት መካከል አንድ ሜትር፤

መ) በሎት ጫፍ እና በጣሪያ መካከል በቂ የአየር ዝውውር

door, which should be renewed regularly;

9) Equipped with humidity meter and thermometer.

10) Loading and unloading area

The loading and unloading area of the warehouse must meet the following requirements:

a) A sheltered loading/unloading area at the door;

b) A sloping ramp that serves for forklifting and for hand-driven carts is required at one of the doors;

c) Trucks should not enter the store as they may damage the store and the stored seed;

11) Area of the store

Factors that determine the size of a store

a) Lot size determinded by standard;

b) One meter space between the walls and the lots in the four sides of the store;

c) One mater space among lots;

d) 1.5 meters space between the top

ለማረጋገጥ በሚያስችል መልኩ 1.5 ሜ መራቁን፤በሚያረጋግጥ መልኩ የሚወሰን ይሆናል፤

ሠ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ከ "ሀ" እስከ "መ" የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ አነስተኛ መጠን ኖሮአቸው ከፍተኛ ዋጋ ላላቸው የዕጽዋት ዘሮች /ለአትክልት፣ ለመኖ ዘር ክምችት…/ አነስተኛ የመጋዘን መጠን 20 ሜ2 ይሆናል፡፡

ረ) ለችግኝ፣ ለአኩራች ዘር፣ ለቁርጥራጭ፣ ለስራስር ማከማቻ ስለሚሆን መጋዘን የተቆጣጣሪው አካል ኢንስፔክተር በሚሰጠው የሙያ አስተያየት የሚወሰን ይሆናል፡፡

12)የቀዝቃዛ መጋዘን መስፈርት

ሀ) ከ6 ወር በታች የክምችት ቆይታ ባህሪይ ያላው ዘር ሥራ ላይ ለመሰማራት የሚፈልግ ሰው የቀዝቃዛ መጋዘን ሊኖረው ይገባል፤

ለ) በኤሌክትሪክ የሚሰራ ቀዝቃዛ የዘር መጋዘን ከ 4 እስከ 10 ዲግሪሴንቲግሬ መቀዝቀዝ የሚችል ሊሆን ይገባል፤

end of the lot and the roof to ensure adequate air circulation;

e) Subject to the provisions of "a" to "d" of this sub article, the minimum size of the storage for high-value plant seeds/vegetable, forage seed stock.../ shall be 20 $m^2$.

f) The store for seedling, tubers, cuttings, roots, shall be determined by the professional opinion given by an inspector.

12) Requirements for cold storage

a) A person who wants to engage in seed business using a variety with shelf life below six months shall have a cold storage facility;

b) An electric operated cold storage should be able to cool the seeds down to 4 to 10 degrees Celsius.

**ዕዝል 2: መለያ ምልክት ላይ የሚካተቱ መረጃዎች**

- የአምራቹ ሥምና አድራሻ፣
- የሰብል ዓይነትና ዝርያ፣
- ጥራቱ የተገለጸ ዘር የሚል ጽሁፍ፣
- የብቃት ማረጋገጫ ሠርትፊኬት ቁጥር፣
- የዘር ደረጃ፣
- የብቅለት መጠን በመቶኛ፣
- የዘር ንጽህና በመቶኛ፣
- የዘር እርጥበት መጠን በመቶኛ፣
- የተጣራ የዘር ክብደት፣
- የተመረተበት ዓመት፣
- የታሸገበት ቀን፣
- የቆይታው ጊዜ፣
- የሎት መለያ ቁጥር፣
- በኬሚካል የታሸ መሆኑን የሚገልጽ ጽሁፍ፣

**Annex 2: Information to be included on the label**

- Seed producer`s name and address
- Crop type and variety
- Written note that notify the seed is Quality Declared Seed
- Certificate of competency number
- Seed class
- Germination percentage
- Purity percentage
- Moisture content in percent
- Net seed weight
- Year of production
- Date of packaging
- Shelf life
- Lot reference number
- Notification that whether the seed is chemically treated.